# ወ/ት ብርቱካን፣ ፌዴሬሽኑና ደንቡ

*ከንፉ አሰፋ (አምስተርዳም)*

“በዋሺንግተን ዲሲ እየተካሄደ ያለው የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽ በዓል ሶስተኛ ቀኑን ይዟል። እኔ እዚህ አለሁ፣ ተጫዋቾቹም እዚሁ አሉ፣ ግን ህዝቡ የት እንደገባ ለማወቅ ጓጉቻለሁ።” ስትል ነበር አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ አሊሻ ፔተርሰን የ2008ቱን የዋሽንግተን ዲሲ የፌዴሬሽኑን ውድቀት የዘገበችው። ፔተርሰን “ሰው ሁሉ የት ገባ?” ብላ ለጠየቀችው ጥያቄ ምላሽም በዘገባዋ አካትታለች። በዓሉ ከኢህአዴግ መንግስት ጋር ቁርኝት ባለው በሼክ አላሙዲ ስለተደነመ በህዝቡ “ቦይኮት” እንደተደረገ በቪዲዮ የተደገፈ ምስል ጋር ቀርቧል።

የኢትዮጵያ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ እ.ኤ.አ. በ2008 ዓ.ም. ከሼክ አላሙዲ ሶስት መቶ ሺህ ዶላር በመቀበሉ ምክንያት በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ላይ ብዙ ዋጋ መክፈሉ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በወቅቱም እንደተዘገበውም ይህ ተቋም ለሶስት መቶ ሺህ ዶላር ሲል ሶስት መቶ ሺህ ህዝብ ነበር ያጣው። ፌዴሬሽኑ 25ኛ ዓመቱን በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ሲያከብር ዝግጅቱ ምን ያህል ደማቅ ሊሆን እንደሚችል የገመቱት በርካታዎች ነበሩ። ዲሲ ኢትዮጵያውያን በብዛት የሚኖሩበትና በዓሉ የብር ኢዩቤልዩ በመሆኑ በቀን ቢያንስ መቶ ሺህ ሰው ተጠብቆ ነበር።

እውነታው ግን እንደዛ አልነበረም። ሜዳው ባዶ ነበር ማለት ይቀላል። ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ፣ ከም እራብ እስከ ምስራቅ እንደጨው የተበታተነውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያሰባስበውን ይህን ማእከል በብር እዩቤልዩ ክብረ-በዓሉ እንደዚያ ተዳክሞ ስናየው ብዙዎቻችንን እጅግ በጣም አሳዝኗል። 25ኛውን የብር እዩቤሊዩ በዓል በዚያ እጅግ በተዳከመ ሁኔታ ካከበረ በኋላ ፌዴሬሽኑ በታዳሚውም ሆነ በበዓል ዝግጅቱ እየቀዘቀዘ ከመምጣቱ አልፎ ዛሬ ከምንገኝበት፣ የብዙሃኑ ድምጽ በሁለትና ሶስት ግለሰቦች የሚሻርበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

የዚህ ጽሁፍ አላማ ወይዘሪት ብርቱካን በአትላንታ ለሚደረገው ዝግጅት የፌዴሬሽኑ የክብር እንግዳ ለምን አልሆኝችም? የሚለውን ጥያቄ ላማንሳት ውይንም ለመከራከር አይደለም። በርግጠኝነት ላመናገር በፌዴሬሽኑ በክብር እንግዳነት መጋበዟ ለብርቱካን የሚጨምርላት አንዳች ነገር የለም። አለመጋበዝዋም ምንም አይቀንስባትም። የአውሮፓ ህብረት የሳካሮቭ እጩ ተሸላሚ ያደርጋት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጩ አለም ታላቅ ዝናንና ክብርን የተቸረች የህዝብ መሪ ናት ብርቱካን። ይልቁንም ወ/ት ብርቱካን በአትላንታ ተጋብዛ ብትገኝ ኖሮ ለፌዴሬሽኑ ታላቅ ክብር ይሆናል።

የአብዛኛው ድምጽ ከሶስት በማይበልጡ በአንባገነኖች ሲገለበጥ ዝም ብሎ የማየት ሞራል ግን ሊኖረን አይገባም። በፌዴሬሽኑ አባላት አጠቃላይ ጉባኤ በአብዛኛው ድምጽ ያለፈው ውሳኔ በግለሰቦች ከተሻረ በኋላ በፌዴሬሽኑ ድረ-ገጽ ላይ የተለጠፈው መግለጫ ደግሞ የበለጠ የሚያበሳጭ ነው። አስቸኳይ ብሎ ፌዴሬሽኑ በድረ-ገጹ የለጠፈው መግለጫ በከፊል እንዲህ ይነበባል፣ “There was a nomination on the floor, a vote was taken and Judge Birtukan’s nomination narrowly passed.” "ዳኛ ብርቱካን በእጩነት ቀረበች፣ ድምጽ ተሰጠ፣ ቤቱ በጠባብ ድምጽ ብልጫ ብርቱካንን አሳለፈ።" ይላል እንግሊዝኛው በወፐ ሲተረጎም። መግለጫው ይቀጥልና የተውሰኑ የፌዴሬሽኑ ቀደምት አባላት ውሳኔው እንዲቀለበስ ባቀረቡት ሃሳብ መሰረት ውሳኔው መሻሩን ይገልጻል።

ይህ የሰሜን አሜሪካ ተቋም ላለፉት 27 ዓመታት ሲተዳደርበት የነበረው ደንብ፣ ስርዓትና በአብላጫ ድምጽ የተደገፈ ውሳኔ እንዲህ እንደዋዛ በሁለትና በሶስት ሰዎች ሲፈርስ ዲያስፖራውን በእጅጉ አስቆጥቷል። ይህን መሰል መግለጫ በፌዴሬሽኑ ድረ-ገጽ ላይ መለጠፉ ደግሞ አባላቱን ብቻ ሳይሆን ታዳሚዊንም ህዝብ መድፈርና መናቅ ነው መስሎ ነው የታየው።

እዚህ ላይ የበለጠ ትኩረት የሳበው ደግሞ የብዙሃኑ ውሳኔ በግለሰቦች መቀልበሱ ብቻ ሳይሆን ፌዴሬሽኑ በተደጋጋሚ ሲታማበት የነበረው ጉዳይ ገሃድ መውጣቱ ነው። በብዙሃን ድምጽ የጸደቀ መመሪያን ሁለት እና ሶስት ሰዎች ማፍረስ ከቻሉ ተቋሙ ከጅምሩም በተደጋጋሚ ሲባል እንደነበረው በሙስና የተዘፈቀና ዲሞክራሲያዊ ያልነበረ መሆኑን ነው የምንረዳው።

“ፌዴሬሽኑ ለበርካታ አመታት ኦዲት ተደርጎ አያውቅም። ... ከቀድሞ አመራሩ ቢያንስ ሁለቱ ግድያ ሙከራ በማድረግ ወንጀል የፈለጋሉ”... ወዘተ የሚሉትን ዘገባዎች ለግዜው እንተዋቸውና የብዙሃን አባላቱ ድምጽ በነዚሁ ተጠርጣሪዎች መረገጥ ጉዳይ ላይ እናተኩር።

ጥበበ ሳሙኤል ፈረንጅ በሚል ስም ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች ድርጊትን በመደገፍ ሲጽፍ ለመከራከሪያ ያቀረበው የህግ አነቀጽ እንዲህ ይላል፣

“Under the Internal Revenue Code, all section 501©(3) organizations are absolutely prohibited from directly or indirectly participating in, or intervening in, any political campaign on behalf of (or in opposition to) any candidate for elective public office. Contributions to political campaign funds or public statements of position (verbal or written) made on behalf of the organization in favor of or in opposition to any candidate for public office clearly violate the prohibition against political campaign activity.

ይህ በጥቅል ሲተርጎም “በሃገር ውስጥ ገቢ አነቀጽ ቁጥር 3 ክፍል 501 መሰረት [ድርጅቱ] በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማንኛውንም ፖለቲካዊ ቅስቀሳ ማድረግና ጣልቃ መግባት አይችልም... ለፖለቲካ ስራ ገንዘብ ማዋጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።..." ይላል።

ጥበበ ሳሙኤል ፈረንጅ ጽሁፉን በመቀጠልም እንደ ወ/ት ብርቱካን አይነት የፖለቲካ ሰዎችን መጋበዝ የተቋሙን ፈቃድ ሊያስነጥቅ እንደሚችልም ሊነግረን ይሞክራል። ነገሩ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ መሰለ። ፖለቲካዊ ቅስቀሳ ማድረግ ወይንም በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና የሙብት ተሟጋችን የክብር እንግዳ አድርጎ መጋበዝ እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? በቃ ይኸው ነው? ሌላ የለም? ሌላ ከሌለ ይህ አንቀጽ እንደ ወ/ት ብርቱካን ያሉ እውቅ ሰዎችን እንዳይጋበዙ የሚከለክል አንዳች ሃረግ የለውም።

“ፌዴሬሽኑ የሚመራበት ደንብ ነው” የሚሉን እንደዚህ ያሉ ሰዎች የሚያቀርቡት የህግ አንቀጽና ትንተና የራሳቸውን ደገፊዎች እንኳን ማሳመን የማይችል ደካማ ምክንያት ሆኖ ነው ያገኘነው። ለሰው ልጅ ሙብት መከበር ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰዎች እና በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል እየፈጸሙ ባሉ መካከል ያለውን ልዩነት ያለማገናዘብ ችግር አለ እንበል?

ይህ ቁንጽል ሃሳብ በጥቅሉ የሚለን “ወ/ት ብርቱካን የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ነች” ነው። የፊፋ ክብር እንግዳ በመሆን የተጋበዙት ኔልሰን ማንዴላም 'ኮ የኤ.ኤን.ሲ. መሪ ነበሩ።

ፊፋ የ91 አመቱ ኔልሰን ማንዴላን የአለም ዋንጫ መክፈቻ ላይ የክብር እንግዳ አድርጎ በመጋበዝ ብቻ አላበቃም። ማንዴላ የተጋበዙበትን ምክንያት ሲገልጽ - ፊፋ እንዲህ ነበር ያለው፣ "He inspired millions with his determination to crush apartheid. Nelson Mandela will be part of another historic moment."

ወደ አማርኛው ሲመለስ፣ አፓርታይድን ለመደምሰስ የነበረው ቁርጠኛ አቋሙ ሚሊዮኖችን በማንቃት ተምሳሌት ሆኗል። ኔልሰን ማንዴላ አሁን እንደገና የሌላ ታሪካዊ ወቅት አካል ይሆናል። እንደማለት ነው።

ፊፋ አትራፊ ድርጅት አይደለም። ፊፋ የፖለቲካ ደርጀት አይደለም። የሃይማኖትም ተቋምም አይደለም፡፡ ቀደምት የደቡብ አፍሪካ መሪዎችን አይደለም የክብር እንግዳ ያደረገው ፊፋ። 'ማንዴላ ለምን ተጋበዙ?' ብሎ የተናገረ ሰው ነበር እንዴ? ካለስ የሞራል ብቃት ይኖረዋል?

ማንዴላ የክብር እንግዳ ሲሆኑ ይህ የመጀመሪያቸው አልነበረም። እጅግ በርካታ የፖለቲካና ፖለቲካዊ ባልሆኑ ስፍራዎች ላይ የክብር እንግዳ ሆነው ተገኝተዋል። እንደ ማንዴላ ያሉ ለሰው ልጆች ነጻነት ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎችም በበርካታ ማህበራዊ ስብስቦች በክብር ተጠርተው እንደተገኙ የእነ ጋንዲ፣ እነ የጄሲ ጃክሰን፣ የእነ ፕራቲያ ሃል፣ የእነ ሁርታ ዶሎርስ... ማህደር ይነግረናል፡፡ ጋንዲ ለሰው ልጅ ንጻነት ራሰቸውን አሳልፈው የሰጡ የፖለቲካ ሰው እንጂ የሃይማኖት መሪ አልነበሩም። ጄሲ ጃክሰንም እንደዚሁ። ...

ወደ እኛ ስንመለስ፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ በአንድ ወቅት የፌዴሬሽኑ የክብር እንግዳ ነበሩ። ለዜጎች መብት መከበር ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ መሪ። በአንጻሩ ደግሞ የሼክ አላሙዲን ጉዳይም አለ። ሼኩ በፌዴሬሽኑ የክብር እንግድነት ከመሆንም አልፈው የክብር አባል ሆነው ተመርጠዋል።

በኢንተርኔት የተለቀቀ አንድ ቪድዮ፣ አላሙዲን በትግራይ ልማት ማህበር ስብሰብ ላይ በመገኘት ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል "ለመጀመሪያ ጊዜ ኢህአዴግ እንድሆን ያጠመቀኝ አምባሳደር ተወልደ ነው። ለንደን ከተማ ኢህአዴግ በገባ በሁለተኛው ወር ከአሰፋ ማሞ ጋር በመሆን ቤቴ ድረስ መጥተው አጠመቁኝ።"

ሼኩ እንዴትና መቼ እዚህ ዘረኛ ድርጅት ውስጥ እንደገቡ ያብራራሉ። እኚህ ሰው ኢህአዴግ መሆናቸውን በአደባባይ እየተናገሩ፣ ገንዘብ ስለሰጡ ብቻ የፌዴሬሽኑ የክብር አባል ሆነው ተመርጠዋል። ይልቁንም በአለም ዓቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች እየተከሰሰ ያለ ድርጅት (ኢሕአዴግ) ቀንደኛ አባልን መጋበዝ በሞራልም ሆነ በፌዴሬሽኑ ደንብ የሚያስጠይቅ ይሆናል።

ፌዴሬሽኑ እንደነዚህ አይነቶችን የሚገድብ መመሪያ አለው የሚሉን ታዲያ ይህ ለምን አልታያቸውም?

አንዳንዶች ደግሞ ለፈለጉት ወገን የሚሰራ ለማይፈልጉትን ደግሞ የሚገድብ ደንብ የሚሉት አባዜ አላቸው። በደፈናው ብቻ ደንብ... ደንብ... እያሉ ሊያደነቁሩን ይፈልጋሉ።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት DEMOCRACY AND REGULATION በሚል ርእስ የወጣ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ አስቀድመው የተደነገጉ ደንቦች ተግባራዊ መሆን እንዴት እንዳልቻሉ ይተነትናል። የአብዛኛውን ህዝብ ዕለታዊ ፍላጎትና የውቅቱን ሁኔታ ማያንጸባርቁ ከሆኑ ደንቦች ተግባራዊ አይሆኑም ይለናል ዘገባው። በዚህም የተነሳ በተለይ በዩናይትድ ስቴትስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚተዳደሩት ቀድሞ በረቀቁ ውስጠ-ደንቦች ሳይሆን እለት-ተዕለት በሚከናወኑ የህዝብ ውይይቶችና ይህንንም በመንተራስ የአመራር አካላት በሚሰጡት ውሳኔዎች ነው ይላል።

ለማጠቃለል ያህል የወይዘሪት ብርቱካን በአትላንታ የክብር እንግድነት መጋበዝ በፌዴሬሽኑ ደንብ መሰረት ስናየው የሚጻረር ነገር አላገኘንበትም። ከዲሞክራሲ አንጻርም በአብዛኛው ህዝብ ድጋፍ ያገኘ ጉዳይ ነው። ታዲያ ውሳኔው ሊቀለበስ የቻለበት ምክንያት ምን ይሆን?

ልንክደው የማንችለው አንድ እውነታ አለ። ፌዴሬሽኑ የወያኔ ነው ብሎ የመደምደሙ ጉዳይ ውሃ አይቋጥርም። በድምጽ አሰጣጡ ላይ በግልጽ እንዳየነው አብዛኛው የፌዴሬሽኑ አመራር አባላት ጠንካራና ለመርህ የቆሙ ናቸው። ነገር ግን ወያኔ ይህንን ቢያንስ በይዞት ግዙፍ የሆነ ተቋም በከፊልም ቢሆን ለመቆጣጠር ትናንሽ ጣቶቹን በውስጥ አሰርጎ አላስገባም ማለት የዋህነት ይሆናል፡፡ "አክራሪ"

ዲያስፖራውን ለመቆጣጠር፣ አልያም ለማጥፋት በሚሊዮኖች በጀት የመደበው ህወሃት ይህንን ተቋም በምን መልኩ ሊያየው እንደሚችል ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል።

ወያኔዎች ቢቻላቸው ተቋሙን ማጥፋት ይመርጣሉ። አሁን እየታየ ያለው አዝማሚያ ያን ይመስላል። ይህ እንዳይሆን ግን ሁላችንም መረባረብ ሊኖርብን የግድ ነው። "ቦይኮት" የሚባል ነገር ፈጽሞ መታሰብ የለበትም። የተቋሙ ጠላቶች የሚፈልጉት ይህንን ነው። አብዛኛው ወገን ራሱን እያገለለ ሲሸሽ አናሳዎቹ ፌዴሬሽኑን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ስለሚሹ "ቦይኮት"ን እንደሚደግፉት አትጠራጠሩ።

ይህ ተቋም ለነጋዴው፣ ለጥበብ ሰው፣ ለሃይማኖት መሪዎች፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች...ወዘተ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መድረክ እየሆነ የሚያገለግል የዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ተቋም ነው - ፌዴሬሽኑ።

መፍትሄ የሚሆነው ወደሚያሰባስበን ተቋማችን በመሄድ የአጠቃላይ ጉባኤውንና የአብዛኛውን ህዝብ ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን ማስገደድ ነው። አሜሪካ እንደ ዛሬዋ ኢትዮጵያ ህግ የሚቀለድባት ሃገር አይደለችም። ማንም ሰው ከህግ በላይ አይደለም። ያለው ብቸኛ አማራጭ በብዙሃኑ ድምጽ አንገዛም የሚሉትን ማሳመን፣ እንቢ ካሉ ደግሞ በህግና ስርዓት ማስወገድ ይሆናል።